# በኢጣሊን ወረራ የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎ ታሪክ

## ማስታወሻ

ከብርሃኑ ተሰማ

ሁሉም ሰው በአካል ከአንድ ባዮሎጂካዊ ዘር የመጣ ሲሆን በመሃከላቸው ያለው ልዩነት እንደጣት አሻራ የረቀቀና ከሰውነት ቆዳ በበለጠ የጠለቀ ነው። የዚህ ጉዳይ መለያየት ከሁኔታዎች መረዳት እንደሚቻለው በትምህርታዊና ማሕበራዊ ተግባራት ገና በመረጃ አልተገለፀም። ወይም አልታየም። ይህም የሆነበት በአንድ በኩል መንፈሳዊ የሃሳብ ልዩነቶች ፍላጎት እኩል ወደአልሆነ ማሕበራዊ ድርጅቶች እያደጉ በመምጣታቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሰብዕና የታወቀ አበይት ልዩነቶችና ተመሳሳይ የልምምድ ዕቅድ አቅጣጫቸውን (ቦታቸውን) በመሳታቸው ነው። ግን ምንም ቢሆን በሰዎች መሀል ያለውን ልዩነቶች መገመገም እንችላለን። የነዚህ ልዩነቶች ተፈጥሮና አስፈላጊነት ሊካድ አይችልም። የሚካድ ከሆነ ለተወሰኑ ችግሮች የማይስማሙ ሲሆን ብቻ ወይም የፍላጎት መካድ ይሆናል።

በሰዎች መሐከል ያሉ ብዙ የአካል ልዩነቶች ቁመት፣ ክብደት፣ አካላዊ ጥንካሬ ወዘተ. የመሳሰሉት በዲርጊቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው። ማንኛቸውም ጠንካራ ሰው በብዙ ድክመቶች መያዙ አይቀሪም። ሰዎች ታሪክ ከሰሩ በአካላዊ ጥንካሬያቸው ምግባር ሲሆን ፤ እነዚህ ጠንካራ ሰዎችም  የትዕይንት  ተዋናዮች ሳይሆኑ ብሔራዊ ጀግኖች ናቸው።

ነገር ግን ሌላው በሰዎች መሃከል ያለው ልዩነት አለመመሳሰል ብቻ ሳይሆን መለወጥ አለመቻላቸውም የግለሰቦችን ታላቅ አስተዋፅዖ የሚያሳይ ሲሆን፡ ጉብዝና የተጠራቀመ ስጦታ መሆኑንም መረዳት ይቻላል። ናፖሊዮን "በጥንቸል ከሚመራ የአንበሳ ወታደር፣ በአንበሳ የሚመራ የጥንቸል ወታደር የተሻለ ነው።" እንዳለው የጀግና ፅንሰ ሃሳብ በስነ ልቦና ጠቃሚ ሰው እንደሆነና ይህም በታሪክ ውስጥ በችግር ጊዜ ባልታሰበ ወቅት ባልታሰበ ግለሰብ ሊነሳ እንደሚችል ነው።

አርበኛ (Patriot) ከግሪክ ቋንቋ የተገኘ ሆኖ አባባሉም ፓትረስ- አገር ሲሆን ከዚህ በመነሳት ፓትሪዩትዝም የሚለው ቃል ሊመጣ ችሏል።

አርበኛ በታሪክ ስንልም ለተደረገው ታላቅ ሥራና ለነበረው ተፅዕኖ ወሳኝነት እንዲሁም ግለሰቦቹ ባይኖሩ የተከሰተው ክስተት በተለየ መንገድ ሊከሰት ወይም ሊዘገይ ይችል እንደነበረ የምናምንበት ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ የአንድ ዲርጊት ውጤት ጠቃሚነት ሁለንተናዊ የሆነ ስምምነት የለውም። አንዳንድ ግለሰቦች አገራቸው ነፃ ሆነች ወይም

አልሆነች: ጦርነቱን አሸነፉ ወይም ተሸነፉ ወደፊት የአለም መንግስታት በቅርፅ ዲሞክራት ሆኑ ፋሽስት ጠቃሚነቱ አይታያቸውም። ይህ ሁሉ ግን ለችግሩ ቁሳዊ ያልሆነ ነው። መታወቅ ያለበት ግን የተፈለገው ከመከሰት አይቀርም ማንም ከችግሩ ማምለጥ አይችልም።

አርበኞች በታሪክ ውስጥ ያላቸው ሚና በበለጠ ለመረዳት ሁለት ነገሮችን መገንዘብና ልዩነቶችን ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል። አርበኛ አድራጊና የፈጣሪነት ባህሪይ አለው። አንዱ ግለሰብ የፈጠረው ሌላው ሊከውን ይችላል። ሁለቱም አርበኞች ናቸው። አርበኛ በታሪክ ፈጣሪ ሲባል ማንኛውም የሰው ሥራ ተከታታይ ዕድገት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖና ይህ ሥራ ባይከናወን ዕድገቱ ወይም ውጤቱ ተመሳሳይ ሊሆንም እንደማይችል መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩልም ደግሞ አርበኛ በታሪክ አድራጊ ሲባል የማንኛውም ሰው ክንውን ውጤት ጠባይ በግለሰቡ ብቃትና ፈቃደኝነት እንጂ ዲርጊቱ በድንገት የተፈፀመ አለመሆኑን የምንረዳበት ጠባይ ነው። ከዚህ ልዩነት ለመረዳት እንደሚቻለው ባጠቃላይ እምነት አርበኛ ወይም ጀግንነቱን መረዳት የሚቻለው በዲርጊት ምግባር ሣይሆን በምንነቱ ምግባር ነው።

ስለአርበኞች ፍላጎትና እምነት ገና በልጅነት የሚፀነስ ቢሆንም የዚህ ፍላጎት ምንጭ በርካታና ጥልቅ ናቸው። ግን በጠባያቸው ከአንድ የታርክ ዘመን ወደሌላው የተለያዩ ባህርዪ አላቸው። በዘመናችን ለቃላቱና ለዲርጊቱ ያለን ፍላጎት ከምን ጊዜውም በበለጠ ተደማጭነትና ትኩረት እያገኘ መጥቷል። በጦርነቶችና በችግሮች ጊዜ የሕዝብ ዕድል በግልፅ አንድ ወይም ጥቂት ሰዎች በሚወስኑት ውሳኔ ላይ ተመስርቶ ይገኛል።

አርበኞች እንዲነሱ ወይም እንዲፈጠሩ የሕብረተሱ ፍላጎት በቂ ሆኖ መገኘት ስለአለበት የዚህን በቂነት የሚቆጣጠሩ ሁኔታዎች በተለያየ መንገድ ሊታዩ ይችላሉ።

በሁሉም ታላቅ የማሕበራዊ ድርጅት ቅርፅ ውስጥ ለአርበኞች ማቴሪያላዊ ፍላጎት መዘጋጀት መሠረታዊ ሃቅና ባጠቃላይ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የመሪ አስፈላጊነት ነው። በግልፅም ሆነ ድብቅ የመሪነት ቁጥጥር ከሕብረተሰብ ሕብረተሰብ ይለያያል። ግን ሁሉም መሪ የሃላፊነት የውሳኔና የሥራ ማዕከላዊነት ምልክት ነው። መሪዎችን በአመራራቸው ሥር በተሰራው ሥራና በተገኘው ውጤት (ጥሩም ሆነ መጥፎ) የመገምገም ተፈጥሮኣዊ ዝንባሌ ነው።

ሌላው ፍላጎት ምንጭ የሚነሳው አዲሱን ትውልድ ከማስተማር የሚያግድ ዝንባሌ በመሆኑ ሁሉም አገር ትክክለኛ ታሪካቸውንና ስለታላላቅ ሰዎች ማሳውቅ ስለአለባቸው ከዚህ ግዴታ ጋር የተቆራኘ ነው። አንዳንድ የጥናት ባህሎች አርበኛ ወይም ጀግና እንደ አገር አባት ወይም መስራች ይታያል። ለምሳል አብረሃም ለእስራዔላዊያን፤ ሮሙለስ ለሮማዊያን ወዘተ.. ስለዚህ የጥንት ታሪክ ሁሌም ለዛሬው መሠረታዊ ኃይል በመሆኑ በአዲሱ ትውልድ አንደበት ውስጥ በቀላሉ ሊቆናጠጥና የሕብረተሰብን እድገት ልውውጥ ማስረዳት መቻል ፤

የግለሰቦችን  ሚና ያላቸው አስተዋፅዖና የበለጠ እንድታውቅ ይረዳል። ትውልድን ስለጥንት ማስተማር ቋሚ መንፈስ በልጆች ለጋ ጭንቅላት መተው በመሆኑ ይህ ከግለሰቦች ወደ ማህበራዊ ተቋም ተዋረድና በግለሰቦች መሀል ያለው ዝምድና ከሥዕላዊና ተጨባጭ ወደ ረቀቀ ሃሳብ እያደገ ይሄዳል። ያለበቂ ስልጠና የሽግግር ዘመን ቀላል አይደለም። ይህ ያለምንም ጥርጥር የብዙ ሰዎች ራሳቸውን ከማሕበራዊ ኃይሎች ከኢኮኖሚ ሕጎችና ከባህል ዓይነቶች ጋር የሚያጣምሩት ዝንባሌ ነው።

በተጨማሪ  ደግሞ ያለው የፍላጎት ምንጭ ማንም ከችግር ያድን  ሰዎች ሁሌ የሚያድነውን ይፈልጋሉ ፤ ወደ አዳኝ ይጠጋሉ። የፖለቲካዊ ወይም ማህበራዊ ጉዳይ ብጥብጥ (አንድ ነገር በአስቸኳይ መሠረት በሚያስፈልግበት ወቅት) አንድ ሰው ብቅ እንድል ይረዳል። ምንም የፖለቲካ  አመራር ይኑረው ችግሩን ወይም አለመረጋጋቱን ለማርገብ  ያለው ፍላጎት በአኳያው ብጥብጡን እንዲቋቋመው ጠንካራና ጎበዝ እንዲነሳ ጊዜው ይፈቅድለታል። ችግሩ አፋጣኝ በሆነ ቁጥር ለአዳኝ ያለው ፍላጎትም (በፀሎትም ይሁን በጦርነት) የአስፈላጊ ሰው ፍላጎት ይጨምራል። አዳኝም ይባል ፈረሰኛ፤ ነብዩም ይባል ማሕበራዊ ቀያሽ ፤ ተወዳጅ ሥነ ሥርዓተኛም  ይሁን ሳይንሳዊ አብዩተኛ እንደዘመኑና ቡድኑ ስያሜ ሊሰጠው ይችላል። የርስ በርስ ግጭት ባለበት ሕብረተሰብ የዕድገት ፕሮግራም ዕቅድ ሊኖር አይችልም። ዕቅድ ጥሩ ነው። ግን በረብሻ በተወጠረ ዘመን አስተዋሽ የለውም። አደጋ፣ ችግር ባንዣበበት ወቅት ስጋት በአንዳንዱ በር ደጃፍ ይቀመጣል። በአኳያው ዕቅዶች የመሰረት አዋጆችና ቃል ኪዳን ሲሆኑ አዋጆች ተፈፃሚነት ለማግኘት ጠንካራ መሪ ያስፈልጋል። አለበለዚያ ስለ መኖራቸውም ይረሳል። ቃል ኪዳንም ይካዳል። ለሁሉም ማን ሠርቶ ማን ፈጻሚ እንደሚሆን ከመጀመሪያው መዋቅር ላይ የተወሰነ ነው።

እንግዲህ ከላይ ለመጠቋቆም እንደተሞከረው አርበኛ በታሪክ ውስጥ ያለው ሚናና ቦታ የህብረተሰብን ዕድገት ከመመርመር ጋር የሚታይ በመሆኑ በአንድ የታሪክ ወቅት ብቻ ብልጭ ብሎ የሚተፋ አይደለም። እኛም አርበኞችን በብዛት በማፍራት ደረጃ ሃብታሞች በነበርንበት በኢጣሊያን ወረራ ወቅትና ከዚያም በፊት አርበኞቹ የነበራቸውን ቦታ ጠንቅቀን ማወቅ ይገባናል።

ስለሆነም የግለሰቦችን አርበኝነት ማየት የምገባን ከመደብ ወይም ከዘር አንፃር ሣይሆን በፍልስፍናው ግለሰቦች ቦታውን የያዙትና የፈፀሙት ጀብዱ ከታሪክ አደራ አኳያ መሆኑን ነው። አርበኛ ከአንድ የተወሰነ ዘር ብቻ አይነሳም። ወይም ከገዥ መደብ ብቻ አይፈጠም። ግን ከላይ በመጠኑ ለማየት እንደተሞከረው የመሪ አስፈላጊነት ፤ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ትምህርትና በችግር ጊዜ የሰዎች አዳኝ ፍላጎት ወዘተ... መሰረት በማድረግ የሚነሳ ነው።

ከዚህ በመቀጠል ለመመልከት እንደሚሞከረው በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ በተደረገው የአምስት አመት ፍልሚያ ኢትዮጵዊያን አርበኞች ያደረጉት ተጋድሎና የከፈሉት መስዋዕት፤ አርበኞቹ በታሪክ ያላቸውን ሚና በበለጠና በሚገባ ሊያሳይ ስለሚችል ማንኛውም አንባቢ አርበኞቹን በዘር፤ በሃይማኖት፤ በመደብና ጠባብ አስተሳሰቦች ከመመልከት በአንጻሩ ሌላ ተጨማሪ ሃሳቦችን ፈልጎ ታሪካቸው የሚጎለብትበትን ሁኔታዎች መፍጠር ይጠበቅበታል።

ቀጥሎ የሁለተኛው የአለም ጦርነት ዋዜማ አርበኞቻችን የከፈሉትንና ያሣዩትን ወኔ በባዕዳና አስተያየት የነበራቸውን አድናቆት ጭምር ለመመልከት ጠቃሚ ይሆናል።

ከ1928-33 ዓ.ም ያለው አመታት የኢጣሊያን ፋሽስት ቅኝ ለመግዛት ወደ ኢትዮጵያ የዘመተበት ወቅት ነበር። በዚህ ዘመን የኢትዮጵያ አርበኞች በሽምቅ ውጊያና የኢጣሊያን ወታደር በአስቸኳይ እንድንኮታኮት ያደረጉት አስተዋፅዖ ፤ ያሳዩት ድፍረት ትንሽ ብቻ አልነበረም።

የነበረው ገዢ መደብ በተንቤንና በማጨው ጦርነቶች ማሸነፉ፣ የአከባቢው ባለባቶች የራሳቸውን መሪ በመምረጥ ጦርነቱን ቀጥለዋል። ብዙዎቹ ዘመናዊ የጦር ልምድ የሌላቸውና የፊውዳሉ ገዢ መደብ በቂ ድርጅታዊ ዝግጅት እንደሌለው የሚታመን ሆኑ በርከት ያሉ አዲስ ከተከፈተው ሆለታ ወታደራዊ ኮሌጅና ጥቂት ከፈረንሳይ ቅዱስ ሳይር የተመረቁ ይገኙበታል።

በ1928 ዓ.ም ወራሪው የኢጣሊያ ወታደሮች ከኤርትራ ተነስተው የመጀመሪያውን ድል በደቡብ ምስራቅ ግንባር ቢቀዳጅም እንቅስቃሴው እንደተፈለገ አልሰመረላቸውም። አፍሪካን ቅኝ ለመግዛት የተላከው ባንዳ ጦር በሸያሸሊ ሥልጣን ሥር የሚመራው ከፍተኛ ጥቃት ካደረገ በኋላ በደጃዝማች በየነ መርድ ተሸነፉ። ቢሆንም ግን ግራዚያኒ ፈቀቅ አላለም። ከደጃዝማች ነስቡ የሐረርጌ ክ/ሃገር ጠቅላይ አዛዥ ከነበረው ጋር የደጃዝማች አምደማሪያም ከአርሲ፤ የደጃዝማች አበበ ዳምጠው ከገሙጎፋ፤ የደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸውና የኃብተማሪያም ኃይሎች ነበሩ።

የራስ ደስታ ኃይሎች በሲዳሞ ሲሸነፉና ወደ አዲስ አባባ የሚያስገባው መንገድ ክፍት ሲሆን ንጉሱ የግራዚያንን ኃይሎች እንዲያጠቃና እንዲበትን ለነስቡ ትዕዛዝ አስተላለፉ። የመጀመሪያው ጥቂት ጦርነቶች ተሳክተውለት ነበር። ደጃዝማች ነስቡ ልምድ ያላቸው ሦስት የውጪ ዜጋ አማካሪዎች ነበሩት። ታሪክ ቤይ ሱዳናዊ የሆነ የኢጣሊያን ወታደር በቲሪፖሊ የተዋጋ፤ ሻለቃ ፋሩቅ በአቴንስ የቱርክ ወታደራዊ አታቼና ውህብ ፓሻ በ1915 ዓ.ም በጋሊፖሊ ጦርነት የከባድ መሳሪያ አዛዥ የነበረ ናቸው። የደጃዝማች ነስቡ ጦር የግራዚያንን ጦር ሲዋጋ ግራዚያን በአውሮፕላን ጋዝ ተጠቀመ። በዚሁ ጦርነት አፄ

ቴውድሮስ ከውጪ ወለደው ተብሎ የሚነገርው በፊውተራሪ ሚሊዮን የሚመራ ጦር የፋሽስቱን ጦር ተቋቋመው።

“Patriotism is a kind of religion; it is the egg from which wars are hatched” Guy De Maupassant, ኢጣሊያ የማስፋፋቱን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴውን የጀመረቺው በሐረርጌ በኩል ሲሆን ግራዚያኒን ያልጠበቀው ጥንካሬ ሲገጥመው ማፈግፈግ ስለነበረበት የኢትዮጵያን ጦር ለመክበብና አጋጣሚዎቹን በመጠቀም ሐረርን መያዝ ተጠራጠረ። ሁለቱም የጦር ግንባሮች ለሌላ ጦርነት እየተዘጋጁ ሳለ ሚያዝያ 23, 1928 ዓ.ም ንጉሱን የያዘው ባቡር ድሬደዋ መድረሱንና ወደ ጂቡቲ አልፈውም እንደሚሄዱ ወሬው ተሰማ። በሁኔታው ደስተኛ ያልሆኑት አራቱ ደጃዝማቾች ነስቡ፣ አበበ፣ መኮንንና አምዴ ጦራቸውን ትተው ንጉሱን ተከትለው ወደ ድሬደዋ መጡ። ፊውተራሪ ሚሊዮን ብቻቸውን ቀሩ። ለመቋቋምም ስላልቻሉ ወደ ጋራሙለታ ተራራ አፈገፈጉ። የግራዚያን ወራሪ ጦርም ሚያዝያ 30, 1928 ጅጅጋን ግንቦት 1, 1928 ሐራርን ተቆጣጠሩ።

ቀደም ብሎ ንጉሱን ይዞ ወደ ጅቡቲ የሚሄደው ባቡር ሚኤሶ ሲደርስ (ንጉሱን እንዲነግሱና የመጀመሪያውን የኢትዮጵያን ሕገመንግስት ለማዘጋጀት ረድተው የነበሩት) በበጅሮንድ ተክለሃዋሪያት እንድቆም ተደረገ። በጅሮንድ ተክለሃይማኖት ከአብዮቱ በፊት ራሽያ የተማሩና ኤደን የኖሩ ሰው ነበሩ። ወደ አገራቸውም ተመልሰው የገንዘብ ሚኒስተር የነበሩና በአንዳንድ ሁኔታዎች ከንጉሱ ጋር ባለመግባባታቸው ጨርጨር ገዢ ሆነው ይሰሩ ነበር። በጅሮንዱም ጠመንጃቸውን እንደያዙ ንጉሱን ሰላምታ ከነሱ በኋላ እንዲከተሏቸውና ወደ ተራራ ወጥተው የአርበኞችን ትግል እንዲያጠናክሩ ጠየቁዋቸው። ንጉሱም ፍቃደኛ ሆነው ሳለ አብረዋቸው የነበሩት ራሶች ግን ስለተቃወሙ በባሩ ተንቀሳቀሰ።

ከጥቂት ጊዜ በኃላ ተክለሃዋሪያት ራሳቸው ለኢትዮጵያ ስደተኞች በልጅ አንዳርጋቸው መሳይ ለሚተባበረው እርዳታ እገዛ ለማድረግ ወደ ጂቡት ሄደው ከንጉሱ ጋር ያላቸውን ልዩነት ሲጠየቁ መልሳቸው “ልዩነታችን ግላዊ ነው ፤ በአገር ጉዳይ አቋማችን አንድ ነው። የሚል ነበር። እንደዚህ ዓይነቱ ከብዙ አባቶች ስለሚሰማ ውጭው ዓለም ኃ/ሥላሴ ተቀናቃኝ የሌላቸው መሪ የሚል አስተሳሰብ አሳድሮላቸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ አበባ ብዙ አደናጋሪና ውዥንብር እየተፈጠረ መጣ። የኢጣሊያ ጦር እየቀረበ መምጣቱ ሲታወቅ ብላታ ተክሌ አዲስ አበባ እንዲትቃጠል ሃሳብ አቀረቡ። ብላታ ኪዳነማሪያም ተቃወሙአቸው። ብላታ ተክሌም “የኢጣሊያን ወታደር የሚንዋጋው ሕዝቡ በነቂስ ሲወጣ በመሆኑ ሕዝቡ ደግሞ የሚወጣው ከተማዋን ሲናቃጥል በመሆኑ ነው” ብሎ መለሰለት ፤ ባላታ ክዳነማሪያምም “እንደዚህ ከሆነ የዓለም ሕዝብ ኃይሉን ማራጋጋት

የሚችለው ኃ/ሥላሴ ብቻ ነው የሚል ግምት ሊያሳድር ይችላል።" ሲለው ተክሌም የዓለም ሕዝብ ጉዳዩ እንዳልሆነ ተናገረ። "ንጉሱ ሄደዋል ፤ ገንዘብ በመኪና ተጭኗል፤ ሱቁ ሁሉ አልተከፈተም፤ ወደ ታላቁ ቤተመንግስት የሚያስከደው ክፍት ነው፤ ባላንበራስ አበበ አረጋይ ለማዳንና ሥነሥርዓት ለማስያዝ ይሞክራሉ" አለ። በከተማው ረብሻና ብጥብጥ ሲነሳ ግን አበበም ሥነሥርዓቱን ማስያዙን ስላልቻሉ ፈረስ ላይ ተቀምጠ እንደነተክሌ ከተማዋን በመደዳው ማቃጠል ጀመሩ።

ሚያዝያ 26, 1928 ዓ.ም ምሽት የኤርትራ የመጀመሪው ብርጌድ የሆነው የኢጣሊያ ጦር አዲስ አበባን ከበባት። በሚቀጥለው ቀን ማክሰኞ የባዶግሎ የሚመራ ጦር አዲስ አበባን ተቆጣጠሯት። ባዶግሎ ሲናገር "በጣም የሚገርም ጉዳይ አጋጠመን። በአጠቃላይ መኖሪያ ቤቶችና ሱቆች በተለይም የአውሮፓዊያኖች ተዘርፈዋል፣ ተቃጥለዋል፣ የሕዝብ መናፈሻዎች ተበላሽተዋል። የንጉሱ ግቢ ሳይቀር ተሰባብረዋል። የንጉሱ ምልክት የሆነው አንበሳም ተገድሏል። ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው ሕዝቡ አረመኔ መሆኑ ነው" ብሏል። ዘረፋውንና ስርቆቱን እናቆማለን በሚል ሰበብ ርሸና ተጀመረ። በቀላሉ 1500

ኢትዮጵያኖች በከራቢንየሪ በተደረገው አሰሳ ተገለዋል። ከከተማ የወጣውን አረጋግቶ ወደ ከተማው ለመመልስ መልዕክት የያዙ በራሪ ወረቀቶች በአውሮፕላን ተረጩ። ሕዝቡ ግን ከመመለስ ወደ ተራራውና ጫካው መጠጋትን መረጡ። ግራዚያኒን ለመርዳት አንድ ባታሊዮን ወደ ሐረር ተላከ። ጦርነቱ በኢጣሊያው ፋሽስት አሸናፊነት ግንቦት 2, 1928 ዓ.ም ሞሶሎኒ ኢትዮጵያ ነፃ የኢጣሊያ ግዛት እንደሆነች ገልፆ ማርሻል ባዶግሎ ጠቅላይ ግዛዥና የኢጣሊያ ተወካይ ሆኖ ተሾመ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባዶግሎ ለሌላ ጉዳይ ሲጠራ ማርሻል ግራዚያኒ ቦታውን ወሰደ።

ኢጣሊያኖች በሁሉም የዜና ማሰራጫዎች ኢትዮጵያኖች በሰላም መኖረ እንደጀመሩ፤ አርበኞች ሁሉ እጃቸውን እንዲሰጡና የኢጣሊያንን ገዢ የሚቃወም እንደሌለ ማናፈስ ጀመሩ። ሐቁ ግን የተለየ ነበር፡ አርበኞች የኢጣሊያንን ማስፈራሪያ ባለመቀበል ወደ ገጠር ተበታተኑ። ብላታ ተክሌ ወደ ሰበታ፤ ደጃዝማች ፍቅረማሪያም ወደ መንዝና ተጉለት፤ ሌሎች ደግሞ ወደ አዋሽ አከባቢ አመሩ። ዮሐንስ ሰመርጀባሻው; "የኢትዮጵያ የብርሃን ምስሶ" የሚል ወረቀት በድብቅ ያዘጋጅ የነበረና ብላታ ክዳነማሪያም አዲስ አበባ መቆየትን መረጡ። ይህም በኋላ ላይ የሴቶችንና የወጣቶችን እንቅስቃሴ ለማጠናከር ረድቷቸዋል። በርካታ አርበኞች እየተያዙ የት እንደደረሱ አይታወቅም የሚባለው ወደ ኢጣሊያ ተልከው ሲሆን ግን ብዙዎቹ የሚናገሩት ከአውሮፕላን ላይ እየተወረወሩ መሞታቸውን ነው። በሐምሌ አቡነ ጴጥሮስ የአርበኞችን ትግል አላወግዝም በማለታቸው አዲስ አበባ ውስጥ ተረሸኑ። ያ ብዙ ኢትዮጵያኖችን አንቀሳቀሰ።

አርበኞችም ትግላቸውን ጀመሩ። አቃቂ ላይ የባቡር ጣቢያዎችን ደበደቡ። በሌላ አከባቢም ራስ ደስታ ዳምጠው በሲዳሞ፣ በጅሮንድ ፍቅረስላሴ በአርሲ፣ ደጃዝማች በየነ መርድ በባሌ፣ ደጃዝማች አበራ ካሣ በሰላሌ፣ በራንበራስ አበበ አረጋይ በምስራቅ ሸዋ፣ ጅማ ሰንበቴ በሰሜን ሸዋ፣ የመሳሰሉት ጠንክረው አከባቢያቸውን በመቆጣጠር የኢጣሊያን ጦር ተከላከሉ። ራቅ ብለው ሐረር አከባቢ በፊውተራሪ በዴና ሌሎች አርበኞች ትግሉ ቀጠለ። በሌላ በኩልም ወሎና አዲስ አበባ ከተያዘ በኋላ ደሴን ከኢጣሊያን ጦር አስለቅቀው እንደገና የፋሽስቱ ጦር በአየር ተደግፎ ተጠናክሮ ሲመጣ ለመልቀቅ ተገደዋል።

የብላታ ተክሌ ጦር ሰበታን እንደተቆጣጠረ ለጦርነቱ ሲዘጋጅ የቤተክርሲቲያን ቃጭልና ብረታብረት በመጠቀም 60 ቼኮዝ በመስራት 15ቱን ለፊውተራሪ ገረሱ ዱኬ ሲልክ በተቀሩት የራሱን ኃይል በማስታጠቅ ለደቡብ ምዕራብ ጦርነት ተዘጋጀ። የፋሽስቱ ባለሥልጣኖችም ከፋፍለህ ግዛን እንደዋና ፖሊሲ መጠቀም ሲጀምሩ ነፃ የወጣችሁ የኦሮሞ ክልሎች ብላታ ተክሌንና ሌሎች የአማራ መሪዎችን ግደሉ፣ እነሱ የንጉሱ ተወካዮች በመሆናቸው የሚወክሉት የአማራውን ሕዝብ ብቻ ነው፣ የሚል ወረቀት በተነ። ግን የብላታ ተክሌ ሚስት ራሳቸው ኦሮሞ መሆናቸውንና አማራና ኦሮሞ በጋብቻ እንደተቆራኙና በጎሳ ላይ የተመሰረተ ልዩነት በመሐከላቸው እንደሌለ አልተገነዘቡትም ነበር።

ኢጣሊያኖችም በዘርና ሃይማኖት ለመከፋፈል ባደረጉት ጥረት ሆን ብለው ኦሮሞን ከአማራ፣ እስልምናን ከክርስትና አስበልጠው ይቀሰቅሱ ነበር። ይህም ሕዝቡን በመለያየት በሌላ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት በመሆኑ እስላሞች መዝግድ እንዲሰሩና ወደ መካ እንዲሄዱ ያበረታቱ ነበር። በዚህም መሠረት ኤርትሪያና ሱማሊያ ጨምሮ ኢትዮጵያን በስድስት ክ/ሃገር በመክፈል የምሥራቅ አፍሪካ ኢጣሊያ ብለው ሰየሚት። የክፍፍሉም ክፍል ትግራይን ጨምሮ የኤርትሪያን ክፍልን በአስመራ ማዕከልነት ፤ አማራ በጎንደር ማዕከልነት ፤ ሸዋን በአዲስ አበባ ማዕከልነት ፤ ኦሮሞ - ሲዳሞን በጅማ ማዕከልነት ፤ አደሬን በሐረር ማዕከልነትና በሐረርጌ ክ/ሃገርን ጨምሮ ሶማሊያን አንድ ላይ በማድረግ ሸነሸኑት። ግን ለሁሉም ግዛት የሥልጣን ምንጭ አዲስ አበባ ላይ ሲሆን በአከባቢ ደረጃም ሥልጣን የተከማቸው በኢጣሊያን ወታደሮችና ፋሽስቱ ባለሥልጣኖች እጅ ነበር።

በሌላ በኩል የንጉሱ ተወካይ ራስ እምሩ ከተንቤን ወደ ጎጃም፤ ከዛም ወደ ጎሬ ከሄዱ በኋላ የተቀሩትን ኃይሎቹን ይዘው ወደ ሱዳን ለመሻገር ሲዘጋጁ “ጥቁር አንበሳ” ተብሎ ከተሰየመው የአርበኞች ቡድን ከድርጅታቸው መሪ ጥሪ ቀረበላቸው። ቡድኑ ዘመናዊና ዲሞክራት የሆነ ሲሆን በብዛት ከሆሎታ ወታደራዊ ኮሌጅ የተመረቁና በዶክተር አለምወርቅ ሊቀመንበርነት የሚመራ እንዲሁም የዶክተር ወርቅነህ መርቲን ልጅና ይልማ ዴሬሳ ወዘተ... የመሳሰሉት የተማሩ ወጣት ኢትዮጵያዊያኖች ይገኙበታል።

የጥቁር አንበሳ ሥራ፣ ታክቲክና ድርጅታዊ አቋም ይታተም የነበረው የድርጅቱ አባል በሆነው በታደሰ ሜጫ ነበር። ከደንባቸው ውስጥ አንቀፅ 2, *"ማንኛውም ሰው አምባገነን መሆን አይችልም"* ፤ የሚል ሲሆን አንቀፅ 3, *"ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም የውጪ ዜጋ ንጉሱን መተካት አይችልም፥ የሚፈልግ ካለ እንቃቃማለን"* ሲል አንቀፅ 4, *"ገበሬዎችን መረበሽና ዝርፊያ የተከለከለ ነው።"* የሚል ሲሆን አንቀፅ 7, ደግሞ *"በኮሚቴው ካልተወሰነ በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ውጪ ለስደት መሄድ የተከለከለ ነው።"* የሚሉ ይገኙበታል። በኢትዮጵያኖች ዘንድ የሚታወቀው ገና ከቴውድሮስ ዘመን ጀምሮ *ማንም ሰው ከተቸገረ ለሌለኛው ፅገዛ ማድረግ የግድ ስለአለበት የቆሰለና መሄድ የማይችል ካለ ራሱን የሚገልበት መሳሪያ ማቀበል አለበት እንጂ ማንም ሰው በሕይወት ጠላት እጅ መግባት የለበትም* የሚል በኮሚቴው አንቀፅ 8, ውስጥ እንደተጠቀሰ ታደሰ ፅፏል። (ይህም ስልሆነ ከጦርነቱ በኋላ በተባበሩት የአለም መንግስታት ሥር ወደ ኮሪያ ዘምተው የነበሩት ከጥቁር አንበሳ ጦርና ከሌሎች ክፍሎች አንዱም እጃቸውን ለጠላት ኃይል ሳይሰጡ በመመለሳቸው አድናቆት አትርፈዋል) ራስ እምሩም በተጠየቁበት በሠረት ሴት ልጃቸውን ወደ ካርቱን ከላኩ በኋላ የኮሚቴውን መሪነት ወሰዱ። ራሱ በሰሜን ክፍል በጣም አዋግተው እንደነበረ ስለሚታወቅላቸው አሁንም በከፍተኛ ጉጉት መፍትሄ ይጠበቅባቸው ነበር።

ይህ አዲስ የተዋቀረው ቡድን የመጀመሪያ ዕቅድ አድርጎ የነበረው አምቦ ላይ ተሰባሰቦ ሥልጠና ካደረገ በኋላ አዲስ አበባን ነፃ ማውጣት ነበር። በዚህም መሠረት በጉዞ ወለጋ ሲደርሱ በኢጣሊያ ተቀስቅሰው የነበሩት የአከባቢው የአገሬው ህዝብና ገዢው ደጃዝማች ውጊያ ከፈቱባቸው። ራስ እምሩም በኃይል ከመግፋት ጉዳዩን ለማስረዳት አንድ ሻለቃ

ላኩ። በዚህን ጊዜ ጦሩ በጉዞ ላይ ሳያውቁ ኢጣሊያን ጦር ውስጥ ገቡ። አርበኞቹም በሳንጃና ካራ ከደበደቡአቸው በኋላ ሦስት ወታደሮች ሞቱባቸው። የቀብር ሥነሥርዓታቸው ራስ እምሩ ባሉበት ሲከናወን ራሱም "እነሱ በሥጋ ቢለዩንም መንፈሳቸው አይለየንም" ብለው በመናገርና በተለይም የሻለቃ በልሁ ከስደተኝነት ከሱዳን መመለስ ሲሰማ የጦሩ መንፈስ ከምን ጊዜ በበለጠ ከፍ አለ። ሻለቃው ሲናገር "በመመለሴ ደስተኛ ሆንኩ፥ አንድ ቀን እሞታለሁ ካርቱም በድሎት መኖር ደስታ አልሰጠኝም ፤ ስለዚህ ደስተኛ ለመሆንና በአገሬ ላይ ለመሞት ተመለስኩኝ ፤ ብሞትና አሞራ ሥጋዬን ቢበላ ያ አሞራ የኢትዮጵያ አሞራ አይደለም? ያ አካሌ ወደ ኢትዮጵያ አፈር አልተመልሰም?" ብለዋል።

በዚህን ጊዜ የሴቶችና ልጆች ስደተኞች እረጨመረ መጣ። ራስ እምሩም የኢጣሊያን ዝግጅትና ነቀምት ውስጥ መሣሪያ እያከማቹ በመምጣታቸው አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን ሲረዱ ኮሚቴው አስቸኳይ ስብሰባ ተጠራና በጉዳዩ ከተወያዩ በኋላ አምቦ ላይ ሊያደርጉ

ያቀዱትን በመሰርዝ ወደ ከፋ በመዝመት የብትወደድ ወልደፃድቅንና ነጋድራስ ወልደሰማያትን ጦር መቀላቀል የተሻለ መሆኑን መረጡ።

በሌላ በኩል ራስ እምሩን እንዳይቀላቀሉ ኢጣሊያኖች አግደውት የነበረው የወለጋ መሪ ብላታ ዴሬሳ ነበሩ። እሳቸውም አምልጠው ሱዳን ከገቡ በኋል የብዙ አርበኞች ስብሰባ ተካፋይ ለመሆን በቅተው ነበር።

የጥቁር አንበሳ ቡድን ጅማ ከደረሰ በኋላ ከኢጣሊያን ጋር ከጊዜ ወደ ጊዜ በርካታ ጦርነቶችን አካሄደ። በዚህን ወቅት እንደ ወለጋው በኢጣሊያን ወታደር የተቀሰቀሱት የጅማው ሱልጣን በቡድኑ እዚያ መገኘት ደስተኛ አለመሆናቸው ሲታወቅ ለቀው ሄዱ። ታደሰ መጫ "እንዴት ወዳጅ እጅ እንደወደቅን" ብሎ ሲፅፍ ከጎጀብ እስከ ቦንጋ ያለውን ጉዞ "ድሃ በሕልሙ ቅቤ ባይበላ እከክ ይወረው ነበር፡" በሚል አባባል አስቀምጦታል።

"No one loves his country for its size or eminence, but because it is own" Seneca to Luciluis. በታህሳስ ወደ 1929 ዓ.ም ራስ እምሩ የፈሩት አልቀረምና እንደተለመደው የሌልት ዘብ ተራውን ጠብቆ እንደወጣ ወዲያውኑ ወዴት ደረሱ ሳይባል በሙሉ ተሰወሩ። ጠዋት ፀሐይ ሲተወጣ የኢጣሊያ ወታደሮች በአከባቢው መታየት ጀመሩ። አንዳዶቹ ለመዋጋት ተዘጋጅቷል። ራስ እምሩ ተዳክመውና እየተቁነጥነጡ በጠላት መከበባቸውን ሲያዩ ኮሚቴውን በድንኳናቸው አከባቢ ሰብስበው እየተወያዩ ሳለ በጅማው ቀኛዝማች በሚመራ ሁለት የኢጣሊያን ወታደሮች መልዕክተኞች ተቋረጠ። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ራስ እምሩን እንዲያነጋግሩት ጠየቁ። እጅ ስለመስጠት ከተነጋገሩ በኋላ ራሱ ለአከባቢው የኢጣሊያን አዛዥ ሶስት የራሳቸውን ወታደሮች መልዕክት አስይዘው አብረዋቸው ላኩ። ግን ብዙም ውጤት አላስገኝም። በኋላ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እጃቻውን እንዲሰጡ ተጠየቁ። ራስ እምሩም ስለራሳቸው እጅ መስጠት ከመወያየት በፊት ወታደር ያልሆነው ሕዝብ ከአከባቢውን ለቆ እንዲሄድ የመውጪያ በር እንዲከፈትላቸው ጠየቁ። የኢጣሊያኖቹ አዛዥም በሁኔታው ከተስማማ በኋላ ሴቶች፣

ሕፃናትና ደካሞች እንዲወጡ ተስማሙና ወጡ። የተጠየቀው ከተሟላ በኋላ አርበኞቹ እጃቸውን ላይሰጡ ይችላሉ በማለት ጠርጥረው በአስቸኳይ እጃችሁን ካልሰጣችሁ በማርታር፣ በቦምብና በመርዝ ጋስ በመጠቀም ሕዝቡን እንፈጃለን የሚል ማስጠንቀቂያ ላኩባቸው። ራስ እምሩ ኮሚቴውን ሰበሰቡና "ረዥም መንገድ አንድ ላይ መጥተን አሁን እንዴት እንድሪግ?" ብለው ጠየቁ። አንዳዶቹ ወታደራዊ ዕቅዳቸው አለመሳካቱን ሲያዩ እጃን ይስጡ አሉዋቸው። "እስብበታለሁ" አሉ። የኢጣሊያን አዝዥ በጋስ ሰፈራቸውን አቃጥል ሌሎቹንም እንዲትፈጅ የሚል ቴሌግራም ከግራዚያን ስለደረሰኝ ቶሎ ብለህ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ እጅህን እንዲትሰጥ የሚል መልዕክ ደረሳቸው።

ራስ እምሩም እንደገና ኮሚቴውን ከሰበሰቡ ብኋላ ከኛ ጋር እየተዋጉ ያሉትን ኤርትራኖችንስ እንዴት እናድርግ ብለው ጠየቁ። (ኤርትራኖቹ የኢጣሊያን ወታደሮችን ከድተውና የኢጣሊያን አገዛዝ በመቃወም የሚዋጉ በመሆናቸው እጃቸውን ከሰጡ ለነሱ የሚሰጠው ቅጣት ከፍተኛ ስለነበረ ነው።) ከዚያም በነሱ ማምለጥ ከተስማሙ በኋላ ጥሩ ጥሩ መሳሪያ (ጠመንጃ) ተመረጠና ኤርትራኖቹ እንዲታጠቁ ተደርጎ በአንድ በኩል ከበባውን ጥሰው እንዲወጡ ተወሰነ። ዕቅዱም የተሳካ ሆነላቸው። እነሱም ገሙጎፋ ደርሰው ከደጃዝማች ገብረማሪያም ኃይል ጋር ተቀላቀሉ። ከዚያም ግንባሩ ወደ ኬኒያ እስከተሰደደ ድረስ አብረው ተዋግተዋል። ራስ እምሩም የቀረውን መሳሪያ እንዲወድም ካደረጉ በኋላ ኃ/ሥላሴ የላከላቸውን ሽጉጥ ባዶ አድርገው በቁሎአቸው ላይ ወጥተው የቀሩትን አርበኞች ይዘው ወደ ኢጣሊያ ጦር ሰፈር አመሩ።

ከአጠገባቸው ያለው አንደኛው ቀኝ እጃቸው የሆኑት ቀኛዝማች ደጀኔ ሆን ብለው የኢጣሊያን ባለማዕረግ ወታደር ሙሉ ልብስ ለብሰው ነበር። ታደሰ መጫ ስለዚህ ጉዳይ ሲፅፍ "ማዕረጉ የሚያንፀባርቅ ነበር። እኛን ምንም አልመሰለንም። እነሱ ሲያዩት አንቀጠቀጣቸው 'ከየት አገኘህ?' አሉት። ቀኛዝማቹም 'በጦርነት ነዋ!' አሉዋቸው" 'እንዴት' አሉት፤ 'ለአለቃዬ ራስ እምሩ ሲዋጋ ያዝኩት' አሉዋቸው። 'ባለቤቱ አሁን የት ነው ያለው' ብለው ጠየቁት። ቀኛዝማቹ ያለዘዴ ወኔ በተሞላ ድፍረት 'እኔ ከያዝኩት በሕይወት የሚኖር ይመስላችኋል? ገደልኩት' አሉዋቸው። የእጅና የእግር ብረት ካስገቡባቸው ብኋላ ወደ እስር ቤት ወሰዱዋቸው። ቀኛዝማቹ በዘበኛ ሲቀልዱ 'አልታጠቅንም እንደሴት ያዛችሁን አሁን እንደ አንበሳ በመሳሪያ ትመሩናላችሁ።' በማለት አሾፉባቸው። ድፍረታቸውም ለሕይወታቸው መጥፋት ምክንያት ሆኗቸዋል።"

የራስ እምሩ መያዝ ለመላው ኢትዮጵያ በዜና ማሰራጫዎች ተላለፈ። ተከታዮቹ በሙሉ እጅ እንዲትሰጡ ወደ መጣችሁበት አከባቢ እንመልሳችኋለን የሚል መልዕክት ተሰራጨ። ሌሎች መሪዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ወደ ኢጣሊያ እንደወሰዱ ሁሉ ራስ እምሩን፣ ይልማ ዴሬሳን፣ ወዘተ.. ወደ ኢጣሊያን አገር ወሰዱዋቸው። ኢጣሊያ ከወሰዱዋቸው ብኋላ ለመተባበር የተስማሙትን ወደ ኢቲያጵያ ይመልሷቸው ስለነበር፤ ራስ እምሩ መናገር ፍቃደኛ ስላልነበሩ ለትብብሩ አልታጩም።

በሌላ በኩል ብላታ ተክሌም በከፋ ውስጥ ተከበው ከሦስት ሳምንት ውጊያ ብኋላ 130 ጦር ብቻ ቀሩዋቸው። በዚህም መሰረት ለማፈግፈግ ተገደው በጅማ ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ሌሎች አርበኞችን ለመቀላቀል ወደ ተራራ አመሩ።

በማንኛውም ወቅት ጊዜና ቦታ ለአንድ ክስተት ተቃራኒው መፈጠሩ አያስደንቅም። በኢጣሊያው ጦርነት አገር ወዳጆችና ለወገን ተቆርቋሪዎች ለጠላት አንበገርም፣ አንገዛም

ብለው መሰዋዕትነት ሲከፍሉ በአኳያው ደግሞ ለጥቅም ተገዥዎችና ከሃዲዎች ከአገር ደህንነት በፊት የራሳቸውን ፍላጎትና ዓላማ ለማሟላት ሲሉ ከጠላት ተባረዋል። እንደነ ራስ ልዑል ራስ ኃይሉ ያሉ በኃ/ሥላሴ ከአገር ገዢነት ተሸረው እስር ቤት ከቆዩ በኋላ ስደት ከመሄዳቸው በፊት ከእስር ቤት ለቀዋቸው ይዘውት ለመሄድ ሲሉ ልዑል ራስ ኃይሉ የጎጃም ንጉሥ ለመሆን ፍላጎታቸው አንፃር አምልጠው ቀርተዋል። በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ጎጃምን ለመግዛት ምናልባትም ከትግራይ ደጃዝማች ካሣ እንዲሁ የውጪ ወራሪዎችን በመጠቀምና ከቴውድሮስ ሞት በኋላ ንጉሥ ዮሐንስ እንደሆኑ ጋር ራሱን ስለሚያወዳደር ነበር። ሆኖም ግን ልዑል ራስ ኃይሉ አርበኞችን ተቀላቅሎ ኢጣሊይንን ያልተዋጋው ከሥልጣን ፍላጎት እንጂ ቅኝ ግዛትን በመደገፍ እንዳልነበረ አንዳንዶች ይናገራሉ። ለዚህም ቀደም ብሎ ለአንዲት እንግሊዛዊት ሴት “ለግብፅ ብዙ ነገር ሰርታችኋል ግን የአገሩ ሕዝብ ራሱ እንዲሰራ ያስተማራችሁት የለም፤ ለአንድ አገር በባዕድ እንደ ወተት ታልቦ መመገብ ጥሩ አይደለም።” ብሎ እንደተናገረ ተገልጿል። የሆነም ሆኖ የተባባሪዎች በኢጣሊያ ሥልጣን ተዋርድ የመጀመሪያውን የያዘው ልዑል ራስ ኃይሉ ሲሆን በሁለተኛነት ደረጃ ደግሞ የንጉስ ዮሐንስ ልጅ ልጅ የሆነው የትግራዩ ራስ ስዩም ነበር። ቀድም ብሎ ከፍተኛ ስልጣን ለማግኘት ወደ ኢጣሊያ ባለሥልጣኖች እጁን ዘርግቶ የነበረው ደጃዝማች ኃ/ሥላሴ ጉግሳ በሦስተኛነት ደረጃ ሲገኝ ደጃዝማች ኃ/ማሪያም የወለጋን ንጉሥነት የወሰደው ቀደም ብሎ ከኢጣሊያን ባለሥልጣኖች ጋር ቢሯሯጥም የትኛው ወገን ጥሩ እንደሆነ ለመረዳት አቅቶት ሲያመነታ ነጋበት። ራስ ጌታቸው በኢየሩሳለም ከኃ/ሥላሴ ጋር ባለመግባባት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ከኢጣሊያን ጋር ተስማምቷል። ሌላው ፀሐፊው ፕሮፌሰር አፈወርቅ ከኢጣሊያን ጋር በመተባበሩ በከሃዲነት ተከሶ እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ድረስ በግዞት የኖረ ሰው ነበር።

ራስ እምሩ ከተያዙ በኋላ ኢጣሊያኖች ጋምቤላን በመያዝ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ግዛት በቁጥጥራቸው ሥር እንደሆነ አናፈሱ። ሕዝቡን ለመደለልና በሥራ ለመወጠር የኢኮኖሚ ዘመቻ በሚል ሰበብ መንገድና ሌሎች የኮንስትራክሽን ሥራ ያሰሩዋቸው ጀመር። ግን አርበኞቹ ለግራዚያኒ የራስ ምታት ከመሆን አንዴም አልተቆጠቡም። ከአርበኞች ትግል ውስጥ በጣም አስደናቂ ከሆነው አንደኛው የሸዋዎቹ አርበኞች አዲስ አበባን ለመያዝ ያደረጉት ጦርነት ነበር። የደጃዝማች አበራ ካሣ ጦር በሰሜን በኩል አዲስ አበባ ገብተው የአውሮፕላን መርዝ ጋስ መቋቋም ስለአቃታቸው ለቀው ሲወጡ በደቡብ ምዕራብ አዲስ አበባ የአድዋው ጀግና የደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ፣ የግራዝማች ዘውዴ አስፋውና የታላቁ መሪ የደጃዝማች ፍቅረማሪያም ጦር ማስለቀቁን ሞከሩ። አንድ ቦታ ላይ አንዳንድ የፍቅረማሪያም ጦር አባላት በኢጣሊያው መሳሪያ ክምችት ተገርመው ፍቅረሥላሴን ማጥቃቱን አቁመን ዝግጅት እናድርግ ሲሉት “ማጨውን ያጣነው እንዲህ አድርገን ነው

ቀጥል ተዋጋ ይህ ሴሊት ሠርጋችም ነው" ብሎ ሲመልስላቸው በመበረታታት መሐል ከተማ ላይ ታላቁን ቤተ መንግሥት ለመያዝ የተቃረቡበት ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር።

ወደ 1929 ዓ.ም አጋማሽ ላይ የምኒልክ ጀኔራል የሆኑት ሽማግሌው ደጃዝማች ባልቻ ታመው ስለነበረ ጅማ አከባቢ ተቀምጠው እዚያ እንዳሉ እጄን ለመስጠት ስለፈለግሁ ከፍተኛ የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች መጥተው እንዲቀበሉኝ የሚል መልዕክት ላኩ። በአንድ አማርኛ ተናጋሪ ባለማዕረግ ኢጣሊያዊ ወታደር የሚመራ ወታደር ቡድን በቦታው ደረሰ። ደጃዝማች ባልቻ መድረሳቸውን ሲያዩ በድንገት ቤልጅጋቸውን ከሥራቸው መዘው ተኩስ ከፈቱባቸው። ብዙ ወታደሮች ገድለው በተኩስ መልሱ ተመተው ሕይወታቸው እስካለፈ ድረስ ሲተረማመሱ ይስቁባቸው ነበር።

የጎንደር ገዢ የነበረው የልዑል ራስ ካሣ ልጅ ከጎንደር በኢጣሊያኖች ከመያዝ ጋር ሞትን ሲመኝ፤ ሁለቱ ወንድሞቹ በሸዋ እየተዋጉ ኢጣሊያኖች እጃችሁን ካልሰጣችሁ በሰላሌ አከባቢ ያለውን ሕዝብ በሙሉ እንፈጃለን ብለው ሲያስጠነቅቁ እጃቸውን እንዲሰጡ በአማላጅነት በመሃል ይመላለስ የነበረው ልዑል ራስ ኃይሉ ሲሆን ማንም አይነካችሁም ብሎ ቃል ገብቶላቸው  የነበረው ሳይከበር ቀረና ሁለቱ ወንድማማቾች ተረሸነው ሬሳቸው ፊቼ ላይ በአደባባይ እንዲታይ ተደረገ። የዚህ ወሬ ሲሰማ በልዑል ራስ ካሣ ልጆች መሞት የተባበሩትንና የተደሰቱትን ለመግደል የመረሃብቴ ገበሬዎች ወደ ሰላሌ ዘመቱ። የሁለቱ አርበኞች መሞት ኢጣሊያኖች እንደገመቱት አመፁን አላቀዘቀዘም። እንዲያውም የአርበኞቹ መሞት ምሳሌ በመሆን ስማቸው እየገነነ ሄደ። ልዑል ራስ ካሣ ከትንሹ  ልጃቸው ጋር እንግሊዝ አገር በስደት ይኖሩ ነበር።

ራስ ደስታ ዳምጠው የኃ/ሥላሴ አማች የነበሩት ቤተሰባቸውን ወደ ውጪ ለስደት በመላክ ራሳቸው በአገር ውስጥ መቆየትና መዋጋትን መረጡ። በጉራጌ አከባቢ አርበኞችን ለማሰባሰብ ሞክረው በአከባቢው በደንብ ስለማይታወቁ እንደአሰቡት አልሆነላቸውም። በዚህን ጊዜ ታላቅ አርበኛ ከነበረው ከታደመ ዘለቀ ጋር ግንባር በመፍጠር ወደ ሲዳሞ አማሩ። የሲዳሞ ሁኔታ በጣም አስጊ ስለነበረ ታደመ ወደ ኬኒያ አለፈ። ራስ ደስታ እየተዋጉ የጥይት እጥረት ሲገጥማቸው ወደ ሲዳሞ ተራራዎች አፈገፈጉ። ከዚያም ወደ አዋሽ ወንዝ ደርሰው ከኢጣሊያን ወታደር ጋር በተደርገው ጦርነት ቆስለው ሲያዙ ኢጣሊያኖች ከግንድ አቆራኝተው ረሸኑዋቸው። ቀደም ብሎ ግራዚያኒ ራስ ደስታንና ደጃዝማች ገ/ማሪያምን ለማዋጋት ብለው ደጃዝማች ገ/ማሪያም ራስ ደስታን ካባረረ ሲዳሞን ለደጃዝማቹ እንደሚሰጡ ወረቀት በትነው ነበር። ይህም የሆነበት ቀደም ብሎ ኃ/ሥላሴ ደጃዝማች ገ/ማሪያምን ሽረው ሲዳሞን ለራስ ደስታ ሰጠተው ነበር። ግን ደጃዝማች ገ/ማሪያም አርበኛ ስለነበሩ ጥሪውን አልተቀበሉትም። ትግሉና ጦርነቱ በየቦታው እንደቀጠለ ሆኖ በሽምጥ ሸለቆ ሐይቅ አከባቢ በተደረገው ከፍተኛ ትንቅንቅ ሁለቱ

ደጃዝማች ገ/ማሪያምና ደጃዝማች በየነ መርድ የፋሽስቱ ጦር ሸምቆ ገደላቸው። ፊውተራሪ ሽመልስም በዚህን ጊዜ ነበር ሕይወታቸውን ያጡት። በጦርነቱ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት በኢጣሊያ ጦር ነበር; የኢጣሊያ ጦር ችግር የነበረው ቁስለኞችን ወደ ጅቡቲ ለመላክ የሚጠቀሙበት ከአዲስ አበባ ድሬደዋ ባቡር ስለነበረ አርበኞች መንገድ ሸምቀው በባቡር ላይ አደጋ ስለሚያደርሱ የበለጠ ለችግሩ የተጋለጡ ነበር። የሁለቱ ደጃዝማቾች መሞት ሕዝቡን የበለጠ ሲቀሰቅስ ሌላው ንዴትን እያባባሰ የመጣው የሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን እየተስፋፋ መምጣት ሲሆን የካህናት በትግሉ ውስጥ መሳተፍና አርበኞችን ማበረታታት ሕዝቡ በበለጠ ለነፃነት ውጊያው እንዲያግዝ ረድቷል።

የአቡነ ጴጥሮስ መገደል፣ ከዚያም አርበኞችን አበረታታዋል ተብለው አቡነ ሚካኤል የሞትን ፅዋ ቀምሰዋል። ብዙ ቄሶችና ዲያቆኖች ለአገራቸውና እምነታቸው በማለት ሕይወታቸውን ሰውተዋል። ግብፃዊው ጳጳስ እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ተባብረው ግራዚያኒ ላይ በተደረገ የግዲያ ሙከራ ቆስለው ወደ ኢጣሊያ ተወስደው ዳግም ወደ ኢትዮጵያ አልተመለሱም። በሌላ በኩልም እስልምና በበለጠ እንዲስፋፋ ሲጥሩ አቤተክርስቲያኖችን በመውረር ካህናትን ያስፈራራሉ፤ ያስራሉ። ዝቋላንና በተለይም የደብረሊባኖስ ገዳም ሲወሩ መሳሪያ በማግኘታቸው ከ350 በላይ መናኩሴዎችን በመግደል ሬሳቸውን ወደ ገደል ተወርውረዋል። ግራዚያኒ በዚህ ድርጊቱ በመዝናናት “ካህን የሚባል አልተረፈም” ሲል ለአለቃው ሞሶሎኒ ቴሌግራም እንዳደረገ ከራሱ ማስተዋሻ ለመረዳት ተችሏል። ውዥንብሩን በመቀጠል በ1930 መጀመሪያ ላይ አቡነ አብረሃምን የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጳጳስ  አድርገው ሾሙዋቸው። አቡነ አብረሃም የሸመገሉ፤ በመርዝ ጋስ የታወሩና በአገሪቱ ካሉት ሁለት ጳጳሳት አንዱ ነበሩ። ሌላኛው አቡነ ይስሐቅ ሲሆኑ እሳቸውን እስከተባበሩዋቸው ድረስ እስር ቤት ውስጥ ያስቀመጡዋቸው ነበሩ። በጎጃም ውስጥ ያሉ ቤተክርስቲያኖች በመቃጠላቸው የክ/ሃገሩ ካህናት የራሳቸውን ስኖዶስ ለመከታተል አልቻሉም። በሌላ በኩል የቅዱስ ጊዮርግስ ካቴድራል ታቦት ወጥቶ በራንበራስ አበበ አረጋይ በሚቆጣጠር አከባቢ ሲቀመጥ የቤተክርስቲያኑ ንብረት ደብረ ብርሃን አጠገብ ባለው የጥንት ዋሻ ውስጥ ተቀበረ።

ከግራዚያኒ የቴሌግራም ማስታወሻ መረዳት እንደተቻለው አብዛኞቹ አርበኞች እጃቸውን ከመስጠት ተዋግተው መሞት የመረጡ መሆኑን ራሱ መረዳቱን ታውቋል። ለዚህም ነበር ማንኛውም “ተቃዋሚ ቡድን የግድ መደምሰስ አለበት። የተከፈለ አስተዋፅዖ ተከፍሎ፤ በጭካኔ መጥፋት አለባቸው። የተያዙና እስር ቤት ያሉት አርበኞች መገደል አለባቸው።” ማለቱ ሰኔ 5, ከተደረገው ቴሌግራም መረዳት ተችሏል። ግን በትህትና ለተገዙት ስጦታ መስጠት እንዳለበት ስለሚያምን በየካቲት 1929 ዓ.ም ተወዳጅ ለመሆን ለድሆችና ደካሞች ስጦታ እሰጣለሁ ብሎ ባደረገው ጥሪ በግራዝማች ለጥበሉ ገብሬ ለአብረሃም

ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ቦምብ ተሰጥቶ በተደረገው ግራዚያኒን የመገደል ሙከራ የኢጣሊያው ተወካይና ሌሎች በአከባቢው የነበሩ ሲቆስሉ የፋሽስቱ ወታደሮች በከፈቱት ተኩስ ሕዝቡን በጅምላ ፈጁት። ሽማግሌዎች አንካሶችና እንዲሁም የመንግስት ተወካዮች ቆሰሉ። ብላክሸርት የሚባለው የመረጃ ፖሊስ በከተማው ዘልቆ በመግባትና በሌሎች ከተሞች በመበታተን ሕዝቡን ፈጁት። ቤቶችን አቃጠሉ። ሕንፃዎችን አፈራረሱ። የቅዱስ ጊዮርግስ ካቴድሪል ቤተክርስቲያን መስኮቶች ተሰባበሩ። በውስጡ ያሉት ጌጣ ጌጦች ተዘረፉ ተበላሹ። ምን ጊዜም አገርቷ ከአደጋ እንዳትላቀቅ ተደርጎ የተመታች ሲሆን በመቶ የሚቆጠሩ የተማሩ ወጣቶች በዚሁ ሰበብ ሕይወታቸው ጠፍቷል። ብዙዎቹ አገሪቷ ካላት የተማረ የሰው ጉልበት አንፃር ሲታይ የጠፉ ትውልድ ተደርጎ መጠቀስ ይቻላል።

ከየካቲት 12-14, 1929 ከሦስት ቀናት መደዳ ጭፍጨፋ በኋላ የአርበኞች ትግል የበለጠ እየተጠናከረ መጣ። ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረገው አልፎ ሞሶሎኒ ጉያ ደረሰ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን የወረረችበትን አንደኛ አመት ንጉሣዊ በዓል ሊታካሄድ የ21 አመት ወጣት ዘርዓይደረስ የተያዙትን ዋንጫዎች፣ ጎራዴዎችና፣ የባለሥልጣኖች ንብረትን ለሞሶሎኒና ንጉሡ እንዲያደርስ ወደ ሮም ተላከ። ሰልፋ በሚካሄድበት ወቅት ዘርዓይደረስ ኢጣሊያኖች ከባቡር ጣቢያ አንስተው ወደ ኢጣሊያ ወስደው የነበረውን ወርቃማ የአንበሳ ምልክት (Lion fo Judah) ሲያይ አይኖቹ ተርገበገቡ። ለመፀለይ ተንበርከከ፤ ሁለት ፖሊሶች ሊያነሱት ሲሞክሩ መለስ አለና በያዘው ጎራዴ ቀነጠባቸው። አምስት የኢጣሊያ ባለሥልጣኖችን ከገደለ በኋላ በተተኮሰው ጥይት ክፉኛ ቆስሎ ሆስፒታል ተወሰደ። ከጥቂት አመታት ብኋላ በኢጣሊያ ደሴት እስር ቤት አረፈ። የዘርዓይደረስ ስምና ሥራ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለዘላለም የሚኖር ሲሆን፤ ከጦርነቱ በኋላም የባህር ኃይሉ የመጀመሪያ ጀልባ ዘርዓይደረስ ትባላለች።

በኢትዮጵያ የሚካሄደው የጀግኖች ግንኙነትና ጥንካሬ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀጠለ በመሄዱ አርበኞች ሸዋ ውስጥ ተገናኝተው በምስጢር ስብሰባ ለማድረግ ወሰኑ። ለስብሰባው ዝግጅት በአብዛኛው የተደረገው በሻለቃ መስፍን ስለሺ ሲሆን የስብሰባው አላማ አርበኞች በየቦታው ማድረግ ስለሚገባቸውና ጦርነቱን እንዴት በአንድነት ለማቀነባበር እንደሚቻል ዕቅድ ለመንደፍ ነበር። ደጃዝማች ፍ/ማሪያም፣ አበበ አረጋይ፣ ብላታ ተክሌና ሌሎች በአምቦ አከባቢ ተገናኙ። ገና ከበቅሎአቸው ወርደው ዕቃቸውን እንዳራገፉ ልውል ራስ ኃይሉና በኢጣሊያ የሚመራው የኤርትራ ጦር ኃይል ከባሻገር ሲያዩ ጦርነት ከተደረ በኋላ የኢጣሊያው ኃይል ሲያፈገፍግ አርበኞቹ ስብሰባውን ቀጠሉ። የራስ አበበ ባለቤት ነፍሰጡር ሲሆኑ የደጃዝማች አበራ ካሳ ባለቤት ደግሞ እመጫት ነበሩ።

ለስብሰባ ከተቀመጡ ብኋላ የምኒልክ ዘመን ደጃዝማች ሽማግሌ ስብሰባውን መሩና ምርጫ ተካሄደ። በምርጫው መሰረት አበበ አረጋይ ዋና መሪ ሆነው ሲመረጡ፤ ደጃዝማቾ ዘውዴ

አሰፋው፣ የንጉስ ኃይለሥላሴ ልጅ ልጅና ኢሳያስ ደቡቡንና ምዕራቡን የኢትዮጵያ ክፍል እንዲከታተሉና ሕዝቡን እንዲያነሳሱ ሲወከሉ፣ ባላታ ተክሌ ወ/ሃዋሪያት የፖለቲካ ጉዳይ ዋና ፀሐፊ ሆነው ተከፋፈሉ። ባላታ ተክሌ ራሳቸው ሲናገሩ "ለዚህ ሥራ ከእኔ የተሻለ ሰው አይገኝም" ብለዋል። በውሳኔው መሰረት ብላታ ትክሌ ከአንድ ሻለቃ ጋር ወደ ወለጋ ከዚያም ወደ ጎጃምና ጎንደር አልፎ ወደ ካርቱም በመሄድ ለትግሉ ጥረት እንዲደረግ ቀስቅሰዋል። አበበ አራጋይ የቀሩትን መሪዎች በየቦታው በመመደብ ሁሉም የሥራ ድርሻቸውንና የሚጠበቅባቸውን አገራዊ ሃላፊነት እንዲወጡ በቃል ኪዳን ከመለያየታቸው በፊት በቡድን ያወሩ የነበሩት ግራዝማች፤ መስፍን ስለሺና ኃይለማሪያም ማሞ መልዕክት አደረጉና አበበ "እንዴት አድርጌ እነኚህን አረመኔዎችን ልቆጣጠር ነው" ብለው ሲያጉረመርሙ እንደተሰማ  ይነገራል። ይህም ከአርበኞቹ ኃይለኝነት ጋር የነብር መሪ ከመሆን አንፃር የተባለ ነበር።

ይህ ስብሰባ በተለይም የልጅ መርድ መንገሻና የልጅ አቢይ አበበ መገኘት፤ ከተከበሩ ቤተሰብ የመጡ በመሆናቸው ሲያጠናክር፤ የልጅ ኃ/ማሪያም ማሞ ሚያዝያ 27, 1928 ዓ.ም አንዲስ አበባን ለመያዝ ይጓዝ የነበረውን የኢጣሊያን ጦር በመዋጋት የመጀመሪያው ሲሆን የጀግንነት ክብር ሲሰጣቸውና የመጀመሪያው አርበኛ በስብሰባው ላይ መገኘት የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖረው ረድቷል።

"Ask not what your country can do for you, ask what you can for do your country" J-F Kennedy, Inagural Address, 1961

የኢጣሊያን ግፍ አገዛዝ ህዳር ውድቅ መሆኑ ሁሉም እየተረዳው መጣ። ግራዚያኒ የፈለገውና እንደፈለገው አልሆነለትም። እሱም የኢጣሊያ ንጉሣዊ ቤተሰብ በሆነው በአስታው መስፍን ተተካ። እንደደናኔ የመሳሰሉት የእስር ቤቶች ተዘጉ። ጊዜው የኢኮኖሚ ዘመቻ ወቅት ነው በሚልሰበብ የኢጣሊያ ገበሬዎች ቤተሰብ በማስፈር የትብብር ዘመን ቅስቀሳቸውን ቀጠሉ። ይህም ሲሆን አርበኞቹን የዓላማቸውና የኢጣሊያ ፋሽስት ከመዋጋት አላዘናጋም። በተለይም በጎጃም በደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ፣ በደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬና በልጅ በላይ ዘለቀ ጦርነት በበለጠ ተጋጋለ። በላይ ዘለቀ በአንድ ወቅት ላይ ተከታዮቹ ራስ ብለው ሲጠሩት አልቀበልም በማለት "እናቴ ያወጣችልኝ ስም በላይ ነው። ይህ በቂ ነው።" ብሎ ስለተናገረ አስቀይሚቸው እንደነበረ ይነገራል።

በጎንደር፣ ትግራይም ራስ ውብነህ ተሰማ, ደጃዝማች አሰፋ ወጋሪ, ፊውተራር መስፍን ረዳ፤ ሁለቱ ወንድማማቾች ልጅ ደስታና ልጅ ዮሓንስ ማሩ እንድሁም ደጃዝማች ኃይሉ ወንዴ ጦርነቱን ገፋበት። በተንቤን ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ (የዋግሹም ልጅ) አርበኞችን በመምራት ውጊያ ሲቀጥሉ ደጃዝማች ኃይሉን በመጨመር የኢጣሊያንን ጦር አጠቁ።

ደጃዝማች ኃይሉ እስከ ካርቱም እየሄዱ ከአርበኞች በመገናኘት መልዕክትም እንዲተላለፍ አድርገዋል። በመጨረሻ ኢጣሊያኖች ገለውት ራሱን ቆርጠው እየጨፈሩ ለፊውተራሪ ክብረት ለአባቱ ይዘው መጡ። አባቱ ዝም አሉ። ትንሽ ቆይተው "እሱስ ስንት የጠላት ወታደር ገደለ?" ብለው ጠየቁዋቸው። ፊታውራሪው ሃዘን ሳይሆን የደስታ ፊት በማሳየታቸው ኢጣሊያኖቹ በጣም ገረማቸው። ፊታውራሪው በተፈጥሮአቸው ወግ አጥባቂና ሀሳበ ግትር በመሆናቸው የንጉሱን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጠቅልለው ኪሳቸው ውስጥ ተሸክመው የሚሄዱና ወታደሩን ለፎቶግራፉ የሚያንበረክኩ ሽማግሌ ናቸው። ይህም ሆኖ ግን ከጦርነቱ በኋላ በመፈንቅለ መንግሥት ተሳትፈዋል ተብለው በስቅለት ተቀጡ።

ደጃዝማች ገ/ሕይወት የሰሜን ምሥራቅ ትግራዩን እንቅስቃሴ በሩ። በሐረር በኩል ፊታውራር ሚሊዮን ቢያዙም ፊታውራር በዴ ጨምሮ ብዙ አርበኞች ወደ ብሪቲሽ ሱማሊያ ሲገቡ፤ በአርሲ በኩል ደጃዝማች ዓባይና ቀኛዝማች ሰለበ ዓጋ ጠንክረው ተዋጉ። በሲዳሞና በቦረና በራስ ደስታ ዳምጠው መሞት ተበታትነው የነበሩት በቀኛዝማች በየነ፣ በቀኛዝማች ጉደታና ቀኛዝማች በቀለ ሥር በመሰባሰብ የኢጣሊያን ጦር አርበደበዱት።

በሸዋ ጦርነቱ በመቀጠል ኢጣሊያኖች በጀመሩት የሞት ሽረት ዘመቻ ደጃዝማች ፍቅረሥላሴና ጅማ ሰንበቴ ሲገደሉ ባላንበራስ አበበ አረጋይ ጥንታዊቷን የአንኮበር ክልል በመያዝ አላስደፍሪም ብሎ ነፃነቱን ይዞ ቆየ። የደጃዝማች ፍቅረሥላሴ ሬሣ እስከመጨረሻውም አልተገኘም። የወታደሩን ሞራል ላለመግደል መሞቱን ሲረዳ ወደ ገደል ተንከባሎ ጠፋ የሚል ግምት አለ። ወታደሩም ሬሣውን ባለማየታቸው እንዳለ ተቆጥሮ እስከ መጨረሻቸው እንደተዋጉ ይነገራል።

የወለጋው ወላዋዩ ደጃዝማች ኃ/ማሪያም በኢጣሊያኖች ሲገደል የተቃውሞው እንቅስቃሴ የበለጠ እዚያም እየተጠናከረ መጣ። አብዛኛውን የኦሮሞ ደቡብ ክፍል ተጠናክሮ መቆጣጠር የጀመረው አርበኛው ፊታውራር ገረሱ ዱኬ ተከታዮቹ ራስ ብለው ሹመውታል። ገረሱ በጣም ታዋቂና እድለኛም እንደሆነ ይነገርለታ። አንዴ በዝቋላ ተራራ ላይ ከፋሽስቱ ኢጣሊያ ባንዳዎች ጋር በተደረገው ከፍተኛ ጦርነት እጁን ከሰጠ በኋላ ተኩስ በመክፈት ከመሃከላቸው አምልጦ ሲመጣ የኢጣሊያን ወታደር በስህተት እርስ በርሳቸው እንዲዋጉ እንዳስደረገ ይነገርለታል። ከዚያም አምልጦ ሶዶ ገባ። ኢጣሊያኖች ሰበካቸውን ሲነዙ "ገረሱ እንደ አንበሳ የነበረው አሁን እንደ ጥንቸል ሆኗልና አባራችሁ መያዝ አለባችሁ" ሲሉ ማናፈስ ጀመሩ። ብዙ ሳይቆይ ገረሱ የአከባቢውን ሕዝብ በማሰባሰብና በማስተባበር እንደገና እንደ አንበሳ ሆነ። እንግሊዝ በጦርነት ውስጥ ከገባች በኋላ እንኳን ሌሎች በፓራሹት የኮመን ዌልዝ ወታደር እገዛ ሲሹ ገረሱ ራሱን በራሱ በማጠናከር ነፃ የማውጣቱን ዘመቻ እስከ ኦማ ወንዝ ድረስ የጠላት ጦርን በመጥረግ ውጤታማ ሆኖ ተገኝቷል።

የአርሲው ኃይሌ አባመርሳ በገሙጎፋ ጦርነት ሲገደል ቀደም ብሎ እንደተጠሰው ሌሎች በአካባቢው የነበሩት ደጃዝማች ወልደማሪያም፤ ፊታውራራ ታደመ ዘለቀና ዘውዴ አየሉ ከነተከታዮቻቸው ወደ ኬኒያ ገቡ።

የኢጣሊያ ፋሽስት በመዋጋቱ ዘመቻ ብቻ ሳይሆን ብዙ ሴቶች ስለጠላት ጦር እንቅስቃሴ መረጃ በመቀበል፤ ስንቅ በመሰንቅና የውስጥ አርበኛ በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። እንደ ወ/ሮ በላይነሽ ከአርሲ፣ ወ/ሮ አያልነሽ በየነ፣ ወ/ሮ አበደች ጨርቆስ፣ ወ/ሮ ከበደችና የልዑል ራስ ሥዩም (በይለፍ ደህንነት ክህደት የተገደለው የደጃዝማች አበራ ካሣ ባለቤት) ጥቂቶቹ ናቸው። ከሁሉ በላይ ግን የወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ ተጋድሎ እንኳን ወዳጅ ጠላት የሚረሳው አይደለም። ገና በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ ገንዘባቸውን ለቀይ መስቀል በመስጠት በግራዚያን ላይ የመግደል ሙከራ ከተደረገ በኋላ ወደ ሚድትራንያን ደሴት እስር ቤት ተወስደው ሁለት አመት ከታሰሩ በኋላ ሲመለሱ፤ አዲስ ዓለም ውስጥ የኢጣሊያን ወታደር ተገሎ በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ለጥቂት ከሞት አምልጠዋል።

ትግሉንም በመቀጠል አርበኞችን ተቀላቅለው ሲዋጉ እንደገና በዘመቻ ተያዙ። ያሳደጉት ልጃቸው ፊታቸው ሲገደል እሳቸው በአደባባይ ዛፍ ላይ ታስረው ተገረፉ። ከዚያም አምልጠው አርበኞችን በመቀላቀል እስከ ድሉ ድረስ በደብረ ብርሃን አከባቢ በቆራጥነት የተዋጉ ሴት ናቸው። ከድሉ በኋላ በ1938 ዓ.ም ሞተው ተገኙ። አሟሟታቸውም ምስጢራዊ ሆኖ ቀይቷል። የብላታ ተክሌ ባለቤትም ቀስለው ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሲሞቱ፤ ብላታ ተክሌ ራሳቸው አንድ ጊዜ ቤት ወስጥ ተከበው ሲታኮሱ አስራ ሰባት ተከታዮቹ ሲሞቱበት እሱና የልጁ ባለቤት አምልጠው ጎጃም ለመግባት ችለዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆን በአገር ውስጥም ይሁን በውጪ በስደተኞች መሃከል ብዙ ጊዜ ይነሳ የነበርው የውይይት ሃሳብ ከድል ብኋላ ምን ዓይነት መንግስት መመስረት እንደሚቻል በሚለው ነጥብ ላይ ነበር። ብላታ ተክሌ ወደ ሱዳን በሄዱበት ወቅት አብዛኛው ስደተኛ ከዘውድ አገዛዝ ይልቅ የሪፑብሊክ መንግሥት መመስረት እንደሚያስፈልግ ይነገረዋል። ከዚያን አልፎ በዘመኑ የፈረንሳይ መንግስት የሪፑብሊክ መንግስት ስለነበረች በጉዳዩ የፈረንሳይ መንግሥት እንዲረዳቸው ደብደቤ ፅፈው እንደነበረ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎ በዘለቄታው አገሪቷን መቆጣጠር አለመቻሏን ስትረዳ ብርቴን ቀደም ብሎ ኢትዮጵያን እንደኢጣሊያ ግዛት አውቃ የነበርችው ሃሳቧን ለወጠች። በዚህን ጊዜ አንዳንድ አርበኞች እንግሊዞችን በመቅረብ ኃ/ሥላሴን ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመለሱ እንዲያደርጉዋቸው ጠየቁ። ይህ በእንዲህ እያለ ብላታ ተክሌ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በፊታውራር ኃይሉ ክብረት ታላቅ ወንድም ወደ ጎንደር ተወሰዱ። አንዳንዶቹ ልጅ ዮሐንስ

እያሱን እንደመሪያቸው ለማውጅ ተዘጋጅተው ስለ ነበረ ተክሌ ይህን ችግር ለመፍታት ነበር። በወቅቱ የአርበኞቹ መሪዎች ይህን አስመልክተው ለተባበሩት መንግሥታትና (League of Nations) "ለሚመለከተው ሁሉ" በሚል ወደፊት መመስረት ስላለበት የመንግስት አይነትና ጉዳዩን አሳሳቢነት ዘጠኝ መቶ አርበኞች የፈረሙበት ደብዳቤ ልከው ነበር።

የአገሪቱን ነፃነት ከመፈለግ አንፃር የአርበኞችን ፍላጎትና ሞራል እየጨመረ በሄደ ቁጥር የኢጣሊያው ባንዳ ጦር እየደከመና እየመነመነ መጣ። ጀኔራል ቦናኮሪሲ የኢጣሊያውን ምሥራቅ አፍሪካ ብላክሸርት ኃይል ኃላፊ ሲናገር "ከሚያዚያ 1931 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን በወታደሮቻችን ላይ የሚፈፀመው ግድያ ዕለታዊ ተግባር ሆኗል። በጦርነቱ ወቅት በአገሪቷ ውስጥ ያሉ አመፀኞች ሁሉ ለጦርነት የተዘጋጁ ናቸው። ጥላቻ እየጨመረ መጥቷል። እንደ ብርቴን ወይም ፈረንሳይ ያሉ አገሮች ባንዲራቸውን ይዘው ወደዚህ አገር ቢገቡ ወታደር አያስፈሊጋቸውም። ምክንያቱም የአገሪቱ ሕዝብ በሙሉ ተቀላቅለው ይዋጉናል።" በማለት ያለውን ፍራቻ ገልጿል። ለዚህም ነበር ኢጣሊያ ከከረን ሐረር 75 ባታሊዮን በማንቀሳቀስ ለጦርነቱ ስትዘጋጅ 170,000 የኢጣሊያን የቅኝ ግዛት ወታደሮችን ለማሳተፍ ችላለች። በሌላ በኩል ኢትዮጵያን ይረዳሉ ተብለው የተላኩት የብርቴን፤ የናጀሪያ፣ የጎድ ክስት (ጋና) ፣ የሱዳን፣ የደቡብ አፍሪካ፣ የህንድ፤ የቤልጅየም፣ ነፃ ፍሮንት በአንድነት ከ20 ሺህ አይበልጡም ነበር። የተቀረውን ትልቁን ኃላፊነት የተሸከመው የኢትዮጵያ የአርበኞች ኃይል ሲሆን ለቁጥር አዳጋች ነበር። ስለሆነም ደከመን ታከተን ሳይሉ አንዴ በዓለም ገናና ተፈርታ የነበረችው የኢጣሊያ ኃይል አንበርክከው ተዋርዳ እንድትወጣ አደረጓት።

ለዚህም ለመጨረሻ ድል ከሚደረገው ዝግጅት ውጪ ጅቡቲ፣ ብርቴን፣ ሱማሊያ ግዛት፣ ኢየሩሳሌም በስደት ላይ የሚገኙት ኢትዮጵይውያኖች ወደ ኬኒያ ተካተቱ። በኢትዮጵያም በጦርነት የተቆረጡት አማራጭ ሲያጡ በሁለት ቦታ ተከፍለው ወደ ኬኒያ ተሰደዱ። አንደኛው ቡድን ራስ እምሩ ሲያዙ አምልጠው የጠፉትን ኤርትሪያኖችን ጨምሮ የሚመሩት በደጃዝማች ወ/ማሪያምና ፊውተራሪ ታደመ ዘለቀ ሲሆን እነዚህም የኦሞ ወንዝን ተከትለው በምሥራቅ ሩዶልፍ ሐይቅ ኬኒያ ሲገቡ ምግብ አልቆባቸው ከኦሞ ወንዝ ዓሣ እያጠመዱ በመመገብ ጉዞአቸውን ሲጨርሱ፤ ሌላው ቡድን በአፈንጉሥ ዘውዴ አየሉ እየተመራ ካፐንጉሪያን በማለፍ እልዶሪት በመድረስ እስያሎ ላይ ካምፕ መስርተው ሲኖሩ ኢጣሊያኖች ተከትለዋቸው ለመምታት ሲዘጋጁ ወደ ታሸታ ተዛወሩ።

የስደተኞች የበላይ ኃላፊ ዘውዴ አየሉ ሲሆን የኢያሱ ታላቅ ልጅ ግርማ በመሃከላቸው ይገኛል። እሱም ከደቡብ ክፍል ከእስር ቤት ያመለጠ ሲሆን ኬኒያኖች እንደንጉሣዊ ቤተሰብ ይመለከቱት ነበር። ልዑል ግርማ ስደተኛው እንዳለ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ

አዘጋጅተው የአገሪቷ የበላይ ጠባቂ የሆኑት እንግሊዞች ይለፍ ከልክለዋቸው በኋላ ጥቂቶቹን በመያዝ መንገድ ጀምረው የኬኒያ በረሃ በመቋረጥ ለድንበር እንደተቃረቡ ባልታወቀ ምክንያት በባለሥልጣኖች ተይዘው ወደ ካምፑ እንዲመለሱ ተደረጉ። ታዲያ ልዑል ግርማ ኢያሱና ትንሺ ሴት ልጃቸው የኢትዮጵያን ድል ሳያዩ በምግብ መርዝ እዚያው ታሸታ ካምፕ ውስጥ ሞቱ። ብኋላ ሜጀር አበበ ደስታና ሎሬንዞ ትዕዛዝ በኃ/ሥላሴ ተልከው ኬኒያ ከሄዱ በኋላ ስደተኛው የኮመንዌልዝ ወታደሮችን ተቀላቅለው ለድል ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ጠየቁ።

ከስደተኛው መሃከል እንደደጃዝማች ሽፈራው ባልቻ ሌላው የአርበኛ መሪ በጂቡቲና በርበራ አድርጎ ኬኒያ የገባው ክፍሌ ዳዲና ከተማ ይፍሩ የሚገኙበት ሲሆን ሌሎች ልጆች እዛው ያደጉ ናቸው። በኋላ ወደ ኬኒያ የመጣው አርበኛ ብላታ ተክሌ ተ/ኃዋርያት ነበር። ብላታ ተክሌ በንግግሩ ስደተኛውን በመቀስቀስ በጣም ጎበዝ ሆኖ እንግሊዞች ሲያዩት ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ በመገመት ጥርጣሬና ፍርኃት ስለአደረባቸው ተክሌ ፖለቲካ እንዳይናገር በማገድ ሃይማኖት እንዲያስተምር ፈቀዱለት። እንግሊዞች ሃይማኖት ያስተመራል ብለው ሲገምቱ እሱ ግን ስለፍልሰት በማስተማር ስደተኛው ሲነቃቃ ይህም ጦር መልምሎ እንዲያሰለጥን ረድቶታል። ለጠሩ ዋና ኃላፊ የ33 ዓመቱ ሙልጌታ ቡሊን መረጠ። ሙልጌታ ሻምበልና ፈረንሣይኛ የሚናገር ከሆሎታ ወታደራዊ ኮሌጅ የተመረቀና ወደ ሰሜን ማይጨው ጦርነት ከመሄዱ በፊት የኮሌጁ አስተማሪ የነበረ ነው።

በርካታ ቤተሰቦችና የታወቁ የቤተሰብ አባል የሆኑት ወደ ሱዳን ተዛውረው ካርቱም በሚገኘው ሰባር የጦር አካዳሚ ውስጥ የውትድርና ሥልጣን ጀመሩ። ብላታ ተክሌ ግን በእንግሊዞች እዛው ተይዞ ሲታሰር፤ ሙልጌታ ቡሊ ወደ ሱዳን በመሄድ አስራተ ካሣን፣ መርድ መንገሻን፣ አሰፋ ደምሴን፣ አማን አምዶምን፣ መንግስቱ ንዋይን ሲቀላቀል፤ እነልዑል ራስ ካሣ፣ ፊታውራሪ ቢሩና ደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸው ከኢየሩሳሌም ወደ ካርቱም እንዲመጡ ተጠሩ።

በሌላ በኩል ኃ/ሥላሴ ኢጣሊያ ተሸንፋ ከአገር እንዲትወጣና እሳቸው ቶሎ ወደ ሥልጣናቸው የሚመለሱበትን ከመሻት ተቆጥበው አያውቁም። በስደት ከሚኖሩት እንግሊዝ አገር ተመልሰው ሱዳን እንደደረሱ መስከረም 1933 ዓ.ም ሻለቃ ሳንድፎርድ የአገሩን ሁኔታ ለማጥናትና የንጉሱን መመለስ ከሚቃወሙት አርበኞች ጋር ስለሁኔታው ለመወያየት አዛዥ ከበደ ተሰማን፣ ጌታሁን ተሰማን፣ ገብረኤልንና ልጅ መርድ ነጋሽን በማስከተል ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ጉዳዩን በጥሞና ከተመለከቱ በኋላ የጎንደር አርበኞች "አገር ደማቸውን ላፈሰሱት ናት" በማለት የንጉሱን መመለስ ሲቃወሙ፤ በጎጃም በላይ ዘለቀ አሻፈረኝ ሲል መልዕክተኞች ከደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬና ከደጃዝማች ነጋሽ ጋር ለንጉሱ በይለፍ ደህነንት ስምምነት ላይ ደረሱ።

ውንጌትም የኃ/ሥላሴን መመለስ እየተሯሯጠ ሲያሳውቅና ሲያሳምን ከኢጣሊያ ጋር የሚደረገውም ጦርነት እየተጋጋለ ሄደ። የኢጣሊያ ወታደሮች ሞራልም እየወደቀ ሲመጣ የጎጃምን ኃይል የበለጠ ለማጠናከር ሲሉ የሞሶሎኒው ተወካይ የወታደሩን ደመዝ በመጨመር ራስ ኃይሉ ተ/ሃይማኖትን የጎጃም ገዢ በማድረግ እሱ ለረጅም ይመኝ የነበረውን የንጉሥነት ማዕረግ እንደሚሰጡት ቃል ገቡለት። ዕቅዱ ደጃዝማች መንገሻንና ነጋስን (ዘመዳሞች የነበሩ) አቅፎ እንዲይዝ ነበር። እሱም ልጁን ደጃዝማች ማሞን የአከባቢው አዛዥ አድርጎ ከሾመ በኋላ ኢጣሊያኖች ባደረጉት የማጭበርበር ዘመቻ ከደጃዝማች መንገሻ ጋር ቅራኔ ውስጥ እንዲገቡ አደረጉዋቸው።

ጥር 12, ቀን 1933 ዓ.ም በዲንደር ላይ የመሸኛ ሥነሥርዓት ከተደረገ በኋላ ኃ/ሥላሴ ሱዳንን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። በዚህን ጊዜ አብረዋቸው የነበሩት ታላቁ ልጃቸው አፍሰወሰን፣ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ገ/ጊዮርጊስ፣ እቴጌ፣ ልዑል መኮንን የሐረሩ መስፍን፣ ደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸው፣ ደጃዝማች አደፍርሰው፣ ቀኛዝማች መኩሪያ፣ ሎሬንዞ ትዕዛዝና ወ/ጊዮርጊስ ነበሩ።

ጥያቄ ካለ btessema41@yahoo.com